በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 1-28/2024 የሚኖረው ወርሃዊ

## የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ................................................- 3 -
ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ...........................................................................- 4 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...................- 5 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት.................................- 5 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ...........................................................................................................- 5 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..............................- 6 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ..- 7 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..............................- 7 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ........................................................- 8 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...........................................................................................- 8 -
እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...........................................................................................- 9 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በጃንዋሪ የመጀመሪያዉ እና ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም **በአዴት** 3.2፣ 4.2፣ 3.8፣ 4.0፤ **በአዲግራት** 3.5፣ 4.5፣ 4.5፤ **በሐሮማያ** 3.8፣ 3.6፣ 2.2፣ 0.2፣ 4.0፣ 4.8 1.8፣ 3.8፣ 3.0፣ 1.6፣ 1.8፣ -0.4፣-0.4፣ 1.2፣ 2.0፣ 4.4፣ 4.6፣ 4.8፣ 3.4 ፤ **በአለም ከተማ** 3.8፣ 3.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.8፣ 1.8፣ 3.8፣ 3.0፣ 1.6፣ 1.8፣ -0.4፣ 4.6 ፤ **በአምባማሪያም** 4.4፣ 4.6፣ 4.6፣ 4.5፣ 3.8፣4.4፣ 4.0፣ 4.6፣ 4.0፣ 3.6፣ 3.6፣ 4.8፣ 4.5፣ 4.4፣ 4.0፤ **በአርሲ ሮቤ** 3.4፣ 3.0፣ 2.5፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 3.5፣ 2.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 4.0፤ **በባቲ** 4.6፣ 3.6፣ 3.6፣ 4.0፣ 2.6፣ 3.1፣ 3.0፣ 4.0 4.6፤ **ቦሬ** 4.5፣ 3.6፤ **በቡኢ** 3.0፣ 3.8፣ 3.4፣ 2.8፣ 3.0፣ 3.4፣ 4.0፣ 4.6፣ 3.0፣ 3.0፣ 2.6፣ 2.0፣ 2.4፣ 3.6፣ 2.5፣ 2.0 3.4፣ 4.6፤ **በደብረብርሀን** -2.0፣ 1.4፣ 3.6፣ 3.0፣ 1.2፣ 2.0፣ 3.8፣ 3.4፣ 2.0፣ 0.4፣ -0.6፣ 0.2፣ 0፣ 0.2፣ 2.2፣ 3.6፣ 4.8፤ **በዳንግላ** 3.5፣ 4.8፣ 4.5፣ 4.7፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.8፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.0 4.5፣ 3.0 4.0፤ **በደባርቅ** 4.2፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.5፣ 4.5፤ **ደብረ ወርቅ** 4.4፤ **ደብረ ማርቆስ** 4.2፤ **በቢሾፍቱ** 3.0፣ 2.0፣ 2.4፣ 4.0፣ 2.0፣ 3.2፣ 4.4፣ 3.8፣ 1.0፣ 4.0፣1.0፣ 1.1፣ 3.2፣ 3.6፣ 3.0፣ 4.0፤ **በእነዋሪ** 4.0፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.5፤ **በፍቼ** 4.5፤ **በጉንዶ መስቀል** 4.4፤ **በእምድብር** 3.4፣ 4.8፣ 4.6፣ 3.5፣ 3.1፣ 3.5፤ **በጃራ** 4.0፣ **በጅግጅጋ** 1.0፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.8፣ 3.2፣ 1.8፣ 2.4፣ 0.2፣ 0.2፣ 1.0፣ 2.0 0.6፣ 2.4፣ 4.0 4.2፣4.2፣ 4.3፤ **በጅማ** 2.4፣ 4.8፣ 4.8፣ 3.4፣ 4.0 ፤**በማይጨዉ** 4.0፣ 3.2፤ **በመሐል ሜዳ** 1.5፣ 4.2፣ 2.2፣ 4.5፣ 3.2፣ 1.6፣ 4.2፣ 1.2፣ 0.5፣ 4.5፣ 4.0፤ **በሮቤ** 3.8፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.0፤ **በሾላ ገቢያ** 1.0፣ 2.1፣ 3.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 3.1፣2.1፣ 3.8፣ 4፣ 3.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 2.0፣ 2.1፣ 2.0፣ 3.0፣ 4.0፣ 3.1፣4.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 3.0፣ 2.8፣ 4.1፣ 4.2፣ 3.4፣ 4.0፣ 4.0 4.0፤ **በወገል ጤና** -1.0፣ 2.0፣ 1.6፣ 2.0፣ 2.5፣ 4.0፣1.8፣1.6፣ 2.2፣ 1.4፣1.8፣2.2፣ 2.8፣ 3.6፣ 3.6፤ **በወረኢሉ** 4.8፣ 3.6 እንዲሁም **የትኖራ** 4.1 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





**ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**


ጃንዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቴፒ 27.3፣ በሰኮሩ 25.7፣ በወላይታ ሶዶ 14.1፣ በማሻ 12.6፣ በአማን 11.9፣ በማጂ 8.1፣ በብላቴ 7.8፣ ሳዉላ 7.3፣ በቦሬ 7.1፣ በተርጫ 6.5፣ በካቺሴ 6.4፣ በጭራ 6.3፣ በኢጃጂ 6.3፣ በፍቼ 5.9፣ በጊምበ 5.3 እንዲሁም በውራቤ 5.3 ሚሜ የሚደርስ ከ1-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል ከጥቂት የደቡብ ምዕራብ እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛዉ ቀናቶች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 3)፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ
የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ወር በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አስር ቀናት ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ እንደነበር የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለድህረ ሰብልና ለእንስሳት መኖ ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ በጎ ጎን ነበረው። በሌላ በኩል የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደነበረውና ከአምስት ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ የተመዘገበ እንደነበር መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በመጨረሻዎቹ አሥራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብና በተወሰኑ የደቡብ የሀገሪቱ ኪስ ቦታዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ አዎንታዊ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን፤ በተጨማሪም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024


ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383940ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈነው የጃንዋሪ ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት አብዛኛው የሀገራችን ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ቢሆኑም፤ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ ኪስ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር የውሃ ሀብት በመጠኑም ቢሆን አስተዋፅኦ (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ

የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኃላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በመጪው ፌብርዋሪ ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ እና ለዝናብ መኖር ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከእዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የፌብሪዋሪ ወር የሚጠበቀው እርጥበት በልግ አብቃይ በሆኑ የደቡብ መዕራብ፣ የደቡብ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምስራቅ፣ የመካከለኛውና የስምጥ ሸለቆ አጎራባች ስፍራዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚሻሽል የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብልችን አስቀድሞ ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አስፈላጊውን የዘር ግብዓት ከወዲሁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የፌብርዋሪ ወር በባሮ አኮቦ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት ላይኛዉ ተከዜ እና የአፋር ደናክል ተፋሰሶች መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ አስተዋፅዎ ስለሚኖረው በተለይም የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናበ ውኃ በማሰባሰብ እና በማከማቸት የውኃ ሀብትን የማሳድግ ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይመከራል። በአንጻሩ አብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ መካከለኛ እና ታችኛው አዋሽ፣ አባይ፣ ተከዜ እንዲሁም የታችኛው ባሮ አኮቦ ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et